በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

<u>በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በሰሜን አሜሪካ አሕጉረ ስብከት የሰንበት ትምሕርት ቤቶች አንድነት ደቡብ ዞን ጉባኤ አካሔደ።</u>



በሰንበት ትምሕርት ቤቶች አንድነት የደቡብ ዞን ሚያዝያ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. (April 30/2011) የሊቀሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስን በዐለ ንግስ ተከትሎ በገነተ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዳላስ ቴክሳስ ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በሰሜን ምዕራብ አሜሪካ የካሊፎርኒያ ሃገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በተገኙበት የመጀመሪያ ጉባኤውን አካሔደ። በዚህም ዕለት ከአምስት አብያተ ክርስቲያናት የተገኙ ሃያ አምስት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ተዋካዮች የጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል። በጉባኤውም ላይ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት እንዴት እንደተቋቋመና አሁን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጠቀለል ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሪፖርት በወንድም ካሳሁን ከተሰጠ በኋላ “ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃን ተመላለሱ” በሚል ርዕስ በብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከአባታዊ ምክር ጋር ቃለ እግዚአብሔር ተሰጥቷል። በመጨረሻም ከታዳሚዎቹ ገንቢ ሐሳቦች ከተሰሙ በኋላ የመርሃ ግብሩ ፍጻሜ ሆኗል። በሰንበት ትምሕርት ቤቶች አንድነት የዞኖች አከላለል መሰረት በደቡብ ዞን አስራ ሁለት ግዛቶች ይገኛሉ።በዚህ ዞን ያሉ ግዛቶች በቦታ አቀማመጥ በጣም የተራራቁና ሰፋ ያሉ በመሆናቸው ለሁለት መክፈል ግድ ሆኗል። እስካሁን ድረስ ከአስራሁለቱ ግዛቶች አብያተ ክርስቲያናት በአምስቱ ውስጥ ያሉት የገፅ ለገፅ ስብሰባ (ጉባኤ) አካሔደዋል። በቀሪዎቹ ግዛች ተመሳሳይ መርሃ ግብር ለማዘጋጀትም ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ጉባኤው እንዴት እንደተካሔደ የሚያሳይ ፎቶግራፍ አያይዘናል ይመልከቱት፡-





